Seattle Department of Education & Early Learning

**የሲያትል ከተማ Sweetened Beverage Tax (SBT፣ የጣፋጭ መጠጦች ግብር)**
**Prenatal-to-Three Community Grant Program (ከቅድመ ወሊድ እስከ ሶስት የማኅበረሰብ ድጋፍ ፕሮግራም)**
**የ Request for Information (RFI፣ የመረጃ ጥያቄ) ማጠቃለያ ኢጋር**

## መግቢያ

Department of Education and Early Learning (DEEL፣ የትምህርት እና የቅድመ ትምህርት መምሪያ) ከቅድመ ውልደት እስከ ሶስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ላሉ ግለሰቦች የጤና እና የትምህርት ውጤቶችን ለማሻሻል የሚረዱ አገልግሎቶችን ለማቅረብ ፍላጎት ካላቸው ማህበረሰብ ተኮር ድርጅቶች ፕሮፖዛሎችን እየጠየቀ ነው።

ከ 2023-2025 ለታቀደው ለዚህ መዋዕለ ንዋይ ወደ $1.4 ሚሊዮን ዶላር የሚጠጋ በጀት ተመድቧል። ብቁ የሆኑ ተቋማት በዓመት ከፍተኛ $140,000 በጠቅላላው ደግሞ በሁለት ዓመት $280,000 የሚጠይቅ አንድ ፕሮፖዛል ማስገባት ይችላሉ። ድጎማው በሲያትል ከተማ Department of Education and Early Learning (DEEL) አስተዳደር ስር በዚህ Request for Proposal (RFP፣ የፕሮፖዛል ጥያቄ) በኩል ይሰጣል። ይህ Prenatal-to-three year Community Grant Request For Proposal (PN-3 Community Grant RFP፣ ከቅድመ ውልደት እስከ ሶስት ዓመት የማህበረሰብ እርዳታ የፕሮፖዛል ጥያቄ) ለአራት ዋና የትኩረት ነጥቦች ፕሮፖዛሎችን ይፈልጋል፦

1. ጤናማ እና ፍትሐዊ ውልደቶች
2. የወላጅ ጤና እና ስሜታዊ ደህንነት
3. ማሳደግ እና የአፀፋ እንክብካቤ አሰጣጥ
4. መልካም የልጅ ጤና እና እድገት

DEEL በሲያትል ከተማ ውስጥ ልጆች የሚጠብቁ ወላጆችን፣ ከውልደት እስከ ሶስት ዓመት ዕድሜ የሆኑ ልጆች ተንከባካቢዎች እና/ወይም አሳዳጊዎችን የማገልገል ተልዕኮ ያላቸው እንዲሁም ቅድሚያ የሚሰጣቸው ህዝቦችን ማለት ቀለም ያላቸው ማህበረሰቦች፣ ስደተኞች፣ ስደተኖች፣ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ሰዎች፣ እና የእንግሊዘኛ ቋንቋ ተማሪዎችን ለመድረስ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ማህበረሰብ ተኮር ድርጅቶችን (CBOs) ለመደጎም ቅድሚያ ይሰጣል። ስኬታማ ፕሮፖዛሎች የሁለት ዓመት ድጎማ ያገኛሉ።

## ብቁነት እና ገንዘብ አሰጣጥ

በዚህ RFP አማካኝነት ለሚገኘው ድጎማ ብቁ ለመሆን፣ ፕሮፖዛል አቅራቢዎች ከሚከተሉት አንዱን መሆን አለባቸው፦

- ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት (ወይም በጀቱ በድርጅት ስፖንሰር የሚደረግ) ከ 501(c)3 ሁኔታ ጋር (ማህበረሰብ ተኮር ወይም ዕምነት ተኮር ድርጅቶችን ጨምሮ)
- መምሪያው የሚጠይቀውን የውል መስፈርቶች የሚያሟሉ የበጀት ስፖሰር የለዩ እንደ ለትርፍ ያልተቋቋመ ያልተደራጁ የማህበረሰብ ድርጅት ወይም ህብረት ስራ ማህበር፣ ለምሳሌ የማህበረሰብ ህብረት ስራ ማህበር፣ ጥምረቶች እና/ወይም ሌሎች የቤተሰብ ቡድኖች
- ጎሳዎች እና የጎሳ ድርጅቶች

በተጨማሪም፣ ፕሮፖዛሎቹ በሲያትል ከተማ ወሰኖች ውስጥ ለሚኖሩ ተሳታፊዎች አገልግሎቶች መስጠት አለባቸው።

ለዚህ የገንዘብ አሰጣጥ ዕድል ብቁ ያልሆኑ ፕሮጀክቶች የሚከተሉትን ፕሮፖዛሎች ያካትታሉ፦

- ፈቃድ ላለው የልጅ እንክብካቤ ጥራት ያላቸውን ድጋፎች ወይም እርዳታዎች የሚያቀርቡ
- አጠቃላይ የድርጅት ክወናዎችን መደገፍ ላይ ብቻ ትኩረት የሚያደርጉ
- ከቅድመ ወሊድ እስከ ሶስት ላይ ያለ ማዕከላዊ ትኩረት የሆኑ
- የፖለቲካ ማግባባት ላይ ትኩረት ያደረጉ

## የተግባራት መርሐግብር

| ኩነት | Date/Time |
|---|---|
| Request for Proposal (RFP) ይጀመራል | 05/03/2023 |
| የ RFP የመረጃ ክፍለ ጊዜ (ቀድሞ የተቀዳ) | 05/03/2023፣ 6:00 PM ላይ |
| የአንድ ለአንድ የቴክኒካል ድጋፍ ክፍለ ጊዜ | ከ 05/03/2023 እስከ 06/07/2023፣ በቀጠሮ |
| የጥያቄ እና መልስ ክፍለ ጊዜ | ከ 05/03/2023 እስከ 06/07/2023፣ 3:00 PM ላይ |

Seattle Department of Education & Early Learning

| የፕሮፖዛሎቹ የመጨረሻ ቀን | 06/14/2023፣ 3:00 PM ላይ |
|---|---|

## ለፕሮፖዛሎች ማኅበረሰብ ላይ መሰረት ያደረገ ቴክኒካዊ እርዳታ

አቅራቢዎች ፕሮፖዛላቸውን ልምድ ካለው የማህበረሰብ ተኮር አማካሪ ጋር ለማዘጋጀት እንዲረዳቸው ነጻ፣ ቀጥተኛ የቴክኒካል ድጋፍ (TA) ይገኛል። የፕሮፖዛልዎን መነልበት ለመደገፍ፣ ከዚህ RFI ጋር ለመስማማት እና የ RFP ቴክኒካዊ መመሪያ ምልከታ ለማድረግ ለመደገፍ ቴክኒካዊ ድጋፍ መጠቀምን አበክረን እንመክራለን። ቴኪኒካዊ ድጋፍን ለመጠቀም፣ ከስር ካሉት አማካሪዎች ማናቸውንም ለማግኘት እባክዎ ነፃ ይሁኑ።

| TA አቅራቢ | የኋላ ታሪክ እና እውቂያ |
|---|---|
| **Catherine Verrenti** | Catherine Verrenti ማኅበረሰቡ ውስጥ ጥልቅ መሰረት ያላቸውን Community Based Organizations (CBOs፣ ማኅበረሰብ ተኮር ድርጅቶች) ለመርዳት እድል በማግኘቷ በጣም ደስተኛ ናት። Neighborhood House እና YouthCare ጨምሮ ከሃያ ዓመት ተግባራዊ ተሞክሮዋ ያተረፈቻቸውን ክህሎቶች እና እውቀት ትሰጣለች። ይህ ሙያ እርዳታ ማጎልበትን እንዲሁም ሰፊ ባሕላዊ ምላሽ ሰጪ የወጣቶች እድገትን፣ የቤተሰብ ድጋፍን፣ ከት/ቤት ውጪ ያለ ጊዜን፣ ጉዳይ አስተዳደር እና ቤት አጥ ፕሮግራሞችን ማስተዳደርን ያካትታል።<br><br>**እውቂያ፡-** catherine@verrenticonsulting.com |
| **Hassan Wardere** | Hassan Wardere ፕሮጀክት አስተዳደር፣ እውነተኛ የማኅበረሰብ ተሳትፎ፣ አቅም ግንባታ፣ የለውጥ አስተዳደር፣ ስልታዊ እቅድ እና አጋርነቶች፣ ቴክኒካዊ ድጋፍ፣ ወዘተ ላይ ስፔሻላይዝ አድርጓል። Hassan ስልታዊ ሃሳቦች ማጎልበትን፣ ስኬታማ ዲዛይኖች እና ፈጣሪ፣ ብጁ የሆኑ፣ ፍትሃዊ የሆኑ ፕሮግራሞችን እና አገልግሎቶችን ማዋሃድ ሲደግፍ ለቤት ባህሎች ዋጋ መስጠት ላይ ልዩ ስልት ይጠቀማል። እንዲሁም ስደተኛ ቤተሰቦችን ከሚያገለግሉ CBOዎች ጋር በመስራት የካበተ ልምድ አለው።<br><br>**እውቂያ፡-** projects@bulleconsulting.com |

## የቋንቋ ድጋፎች

ተጨማሪ የቋንቋ ድጋፎች የሚያስፈልጉዎት ከሆነ፣ DEEL እርዳታ ሊያቀርብ ይችላል። እባክዎ Tiffany Lee ን በ tiffany.lee@seattle.gov ያግኟት።

## ተጨማሪ መረጃ

የ Grant Program (የእርዳታ ፕሮግራሙ) ሙሉ ዝርዝር መረጃ **Prenatal to Three Community Grant Program Request for Proposal (ከቅድመ ውልደት እስከ ሶስት ዓመት የማህበረሰብ እርዳታ የፕሮፖዛል ጥያቄ)** ውስጥ በዝርዝር ተቀምጧል። ለዚህ የእርዳታ ፕሮግራም ሁሉንም መረጃ እና ማመልከቻ በሚከተለው ማግኘት ይቻላል፦ የ DEEL የገንዘብ አሰጣጥ እድሎች ድረ ገጽ፦ http://www.seattle.gov/education/for-providers/funding-opportunities